ጌታችን ኢየሱስ ላባ ለዮሥፍ ልዮ ከገለጸው።

«እንደ ዓርብ ስቅለት ስግደት፣ በመ
ንፈሳዊነት ይዘውተር። በጸጋ እግዚአ
ብሔር ሆነው ተደፍተው ለሚሰግዱ
ልኝ ሁሉ ብዙ ጸጋና ረድኤትም እሰ
ጣቸዋለሁ።»

«ስግደት ለመስቀል በመላው ዓለም
ላይ ይስፋፋ፤ በዚሁ መንፈሳዊ ተግባር
የእግዚአብሔር መንክራት ይታያሉ።»

«በዚሁ የስግደት ተግባር ቍጥር
የሌላቸው ነፍሳት ይድናሉ።»

«ይህ በመመሠረት ላይ ያለ ማኅ
በር ከሁሉ በፊት በመንፈሳዊነት፣ በመ
ረዳዳት፣ በትሕትና፣ በሥራ፣ በጠና የወ
ንድማማችነት ፍቅር ይታነጽ፣ ፍጻ
ሜውም ከተሰቀለው ኢየሱስ ጋር በደ
ስታ መስቀልህን በመሸከም ይኹን።»

«ይህ በመቋቋም ላይ ያለ ማኅበር
ወደ መላው ዓለም ላይ ተስፋፍቶ እንደ
ፍሬያም ዛፍ ልክ የሌለው ፍሬ ይሰጣል።»

«ከዚህ ማኅበር ብዙ ቅዱሳን እንዲ
ገኙ አደርጋለሁ።»

«ከዚሁ መንፈሳዊ ማኅበር ቅዱ
ሳን ወላጆችና ብዙ መንፈሳዊ ጥሪ ያላ
ቸው ሰዎች እንዲገኙ አደርጋለሁ።»

«ይህ ቅዱስ ማኅበር በስሜ ላይ
የሚነገረውን የድፍረት ቃል ሊክስና ወ
ጣቶችንም እንደ እምላክ ፍላጎት እያስተ
ማረ የዓለምን መታደስ ስለሚያመጣ ወደ
መላው ዓለም እንዲስፋፋ ፍላጎቴ ነው።»

ይህን ጸሎት ለማዘውተርና የክ. ት.
መ. ማ. ዓላማን ለመደገፍ የሚፈልጉ ክር
ስቲያኖች ሁሉ እንደጥሪያቸው ለክ. ት.
መ. ማ. አመልክተው ማኅበርተኞች ሊሆኑ
ይችላሉ።

በቤተ ክርስቲያን አለቆች ፈቃድ፣

በ ተ ሰ ቀ ለ ው ኢ የ ሱ ስ ና
በ ን ጽ ሕ ት ድ ን ግ ል ማ ር ያ ም
የክርስቶስ ትምህርት መምህራን ማኅበር
ኢ ት ዮ ጵ ያ
መከነ መንበረ ኪዳነ ምሕረት
የደብዳቤ ሣጥን ቍጥር 913
አ ሥ መ ራ
አዘጋጅነት የሚታተም።

ሰላም ለመስቀለ ክርስቶስ
ዕፀ መድኀኒት፣ ኀይላችንና ጥግያችን።

የመስቀል በዓል ፲፱፻፺፱ ዓ. ም.




‹... ከምድር ከተነሣኹ በኋላ ሁሉን
ወደ'ኔ እስባለሁ» (ዮሐ፣ ፲፪፣ ፴፪)።

## ስግደት ለተሰቀለው ኢየሱስ ።

አምላክ ሆይ፣ ና አድነኝ፣
ጌታ ሆይ፣ ፈጥነህ ርዳኝ።
ስብሐት።

### ወደ ቀኝ እጁ ቍስል ።

የምትወደደው የተሰቀልህ ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ፣ ከና'ቴ ማርያም፣ ከሁላቸውም መላእክትና ቅዱሳን ጋር ተባብሬ ወደ ቅዱስ የቀኝ እጅህ ቍስል ከልብ ተደፍቼ እሰግዳለሁ። ፈጽሜ የምጸየፈው ኀጢአቴን ልትክስ ብለህ ብዙና የሚያሰቅቅ ሥቃይ በመቀበልህ የገለጽክልኝ ወሰን የሌለው ፍቅርህን እያሰብኹ አመሰግንሃለኹ። ቤተ ክርስትያንህን በተቃራኒዎችዋ ላይ ድል የምታገኝበትና ልጆችዋንም ሁሉ ትእዛዞችህን እየጠበቁ በቅድስና የሚኖሩብትን ጸጋ እንድትሰጥ እለምንሃለኹ ።

አባታችን ሆይ፤ ሰላም፤ ስብሐት።

### ወደ ግራ እጁ ቍስል ።

የምትወደደው የተሰቀልህ ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ፣ ከና'ቴ ማርያም፣ ከሁላቸውም መላእክትና ቅዱሳን ጋር ተባብሬ ወደ ቅዱስ የግራ እጅህ ቍስል ከልብ ተደፍቼ እሰግዳለሁ። ለኀጢአተኞች፣ በሞት ጣር ላይ ላሉትና ይልቁንም ከንተ ጋር ሊታረቁ ለማይፈልጉ ትምራቸው ዘንድ እለምንሃለኹ።

አባታችን ሆይ፤ ሰላም፤ ስብሐት።

### ወደ ቀኝ እግሩ ቍስል ።

የምትወደደው የተሰቀልህ ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ፣ ከና'ቴ ማርያም፣ ከሁላቸውም መላእክትና ቅዱሳን ጋር ተባብሬ ወደ ቅዱስ የቀኝ እግርህ ቍስል ከልብ ተደፍቼ እሰግዳለሁ። ከውሉደ ክህነትና ላንተም ከተሰጡት ሰዎች ውስጥ ብዙ ቅዱሳን እንዲገኙ ጸጋ እንድትሰጣቸው እለምንሃለኹ።

አባታችን ሆይ፤ ሰላም፤ ስብሐት።

### ወደ ግራ እግሩ ቍስል ።

የምትወደደው የተሰቀልህ ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ፣ ከና'ቴ ማርያም፣ ከሁላቸውም መላእክትና ቅዱሳን ጋር ተባብሬ ወደ ቅዱስ የግራ እግርህ ቍስል ከልብ ተደፍቼ እሰግዳለሁ። በንስሐ ቦታ ለሚገኙት ነፍሳትና ይልቁንም በቅዱሳን ቍስሎችኽ ላይ ልዩ መንፈሳዊነት ለነበራቸው ታድናቸው ዘንድ እለምንሃለኹ።

አባታችን ሆይ፤ ሰላም፤ ስብሐት።

### ወደ ጐኑ ቍስል ።

የምትወደደው የተሰቀልህ ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ፣ ከና'ቴ ማርያም፣ ከሁላቸውም መላእክትና ቅዱሳን ጋር ተባብሬ ወደ ቅዱስ የጐንኽ ቍስል ከልብ ተደፍቼ እሰግዳለሁ። በጸሎቴ የሚማጠኑትን ሰዎች ሁሉ እንድትባርካቸውና እንድታዳምጣቸው እለምንሃለኹ።

አባታችን ሆይ፤ ሰላም፤ ስብሐት።

አዛኝቱ ድንግል ሆይ፣
ለምኚልኝ። (፫ ጊዜ)

የተሰቀልህ ኢየሱስ ሆይ፣ በሕማማትህ ትሩፋት ልመናዬን ስማ። በቅድስና እንድኖር፣ በለኝ አቅም ሁሉም መንግሥትህን ለማስፋፋት ራሴን እየሰጠሁ፣ ምሥጢራትህንም ተቀብዬ እንድሞትና በክብርኽም ከንተ ጋር ለዘለዓለም እንድኖር ታደርግ ዘንድ እለምንኽ አለኹ። አሜን።